Arlington
Public
Schools

የልዩ ትምህርት ቢሮ
2110 Washington Boulevard, 2nd Floor
Arlington, Virginia 22204
703-228-6040

# ለገለልተኛ የትምህርት ግምገማ የሚሆኑ መመሪያዎች

በአካል ጉዳተኞች ትምህርት ሕግ (IDEA) መሰረት፣ አንድ ወላጅ በተማሪው የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) በተደረገው ግምገማ የማይስማማ ከሆኑ፣ የተማሪውን ገለልተኛ የሆነ የትምህርት ግምገማ (IEE) በመንግስት ወጪ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ IEE ለተማሪው ትምህርት ኃላፊነት ባለው የLEA ተቀጣሪ ባልሆኑ እና ብቃት ባላቸው ፈታኝ ወይም ፈታኞች የሚካሄድ ግምገማ ነው፡፡ LEA ወላጅ ያልተስማማበትን ግምገማ ባደረገ ቁጥር አንድ ወላጅ በመንግስት ወጪ አንድ IEE ብቻ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

የIEE ጥያቄዎች በአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች (APS) የልዩ ትምህርት ቢሮ በኢሜል በ፡ iee@apsva.us ወይም በፖስታ በ፡ Arlington Public Schools, Office of Special Education, Director of Elementary Special Education, 2110 Washington Blvd., 2nd Floor, Arlington, Virginia 22204 መቅረብ አለባቸው፡፡

የIEE ጥያቄ እንደደረሰ፣ APS ለወላጅ IEE የት እንደሚገኝና ስለሚመለከተው የIEE መመዘኛ መረጃ ያቀርባል፡፡ APS በራሱ ውሳኔ፣ የIEE ጥያቄን በተመለከተ የፍትህ ሂደት ችሎት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

በቨርጂኒያ ውስጥ የአካል ጉዳተኛ ልጆች የልዩ ትምህርት መርሃ ግብሮች የሚቆጣጠሩት ደንቦች ላይ እንቀረበው "… ግምገማው የተገኘበት መስፈርት፣ የግምገማውን ቦታና የፈታኙን መመዘኛዎች ጨምሮ የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ ግምገማ ሲጀምር ከሚጠቀምባቸው መመዘኛዎች ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፡፡"

ከእነዚህ ደንቦች ጋር ተስማሚ በሆነ መልኩ APS የሚከተሉትን መመዘኛዎች አዘጋጅቷል፦

I. ገምጋሚዎች የሚከተሉትን መሆን አለባቸው: -

ሀ. በሜሪላንድ ወይም በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ የሚሰሩ ከሆነ ከቨርጂኒያ የትምህርት ቦርድ ወይም ተመሳሳይ ፈቃድ መያዝ አለባቸው፤ ወይም

ለ. ገምጋሚው በቨርጂኒያ ኮመን ዌልዝ በመስክ ላይ እንዲሰራ ወይም በሜሪላንድ ወይም በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ የሚሰራ ከሆነ ከቨርጂኒያ የጤና ሙያዎች ትምህርት ክፍል አሁን ላይ የሚያገለግል ፍቃድ መያዝ አለበት፡፡

ሐ. አገልግሎት አቅራቢው በማንኛውም ስቴት ውስጥ አሁን ላይ የእገዳ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ወይም ሌላ የስነምግባር ቅጣት ያልተጣለበትን መሆንን ጨምሮ ከሚመለከተው የቁጥጥር አካል ጋር መልካም ሁኔታ ላይ ያለ መሆን አለበት፡፡

መ. ከአርሊንግተን ካውንቲ ቨርጂኒያ በሃምሳ ማይል ራዲየስ ውስጥ የሚሰራ መሆን አለበት፡፡

ሠ. የወንጀል ፍርዶችን በተመለከተ የኮንትራክተር ማረጋገጫ ቅጽ መሙላት ይኖርበታል፡፡

II. ግምገማዎችን በሚካሄዱበት ጊዜ የሚከተሉት ደረጃዎች እና መመሪያዎች መከበር አለባቸው፦

ሀ. የተማሪ ግምገማ ከማካሄዱ በፊት፣ ገምጋሚው በመጀመሪያ በAPS ውሳኔ በቂ ሰነዶችን በማቅረብ ረገድ በአንቀጽ I የተገለጹትን መመዘኛዎች እርካታ ማረጋገጥና ግምገማውን ለማካሄድ ፈቃድ መኖሩን ከAPS ማረጋገጫ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

ለ. ግምገማው የሚካሄደው በቢሮ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ወይም በሌላ ተገቢ ለሙያው አመቺ ቦታ ላይ ነው፡፡ የተሟላ ግምገማውን ለማካሄድ በAPS በተፈቀደለት አካል መከናወን አለበት፡፡

ሐ. ሁሉም ፈተናዎች በግለሰብ ደረጃ መሰጠት ይኖርባቸዋል፡፡

መ. ቀደምት ዝግጅቶች ካልተደረጉና በAPS ካልጸደቁ በስተቀር የቅርብ ጊዜ የፈተናው እትም፣ የደረጃ አሰጣጥ ወይም ሌላ እትም ስራ ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡

ሠ. ሁሉም ፈተናዎች በፈተና መመሪያው ላይ በቀረበው መመሪያ መሰረት መሰጠትና ውጤት መሰጠት አለበት፡፡

ረ. ልኬትን ወይም ክላስተርን ያካተቱ ሁሉም ፈተናዎች ወይም ንኡስ ፈተናዎች መሰጠት ያለባቸው ሲሆን የልኬት ወይም ክላስተር መደበኛ ውጤቶች ሪፖርት መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

ሰ. ፈተናዎች የሚመረጡት እያንዳንዱ ተለይቶ የሚታወቅ የትምህርት ስጋት ቦታ መፍትሄን ለመሻት ነው፡፡

ሸ. ሁሉም ፈተናዎች ዘርና ባህልን መሰረት በማድረግ አድሎ የሌላባቸውና ጥቅም ላይ ለዋለበት የተለየ አላማ መፈተሽ አለበት፡፡

ቀ. የተገደበ የእንግሊዘኛ ችሎታ ያለው ልጅን ለመገምገም የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችና ሂደቶች የልጁን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ከመለካት ይልቅ ህጻኑ ምን ያህል የአካል ጉዳት እንዳለበትና ልዩ ትምህርት እንደሚያስፈልገው ለማረጋገጥ ተመርጠው መሰጠት አለባቸው፡፡

በ. በደረግ የማይቻል ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ፈተናዎች በልጁ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም በሌላ የግንኙነት ዘዴ መቅረብ እና መሰጠት አለባቸው፡፡

ተ. ፈተናዎች መምረጥና መሰጠት ያለባቸው ውጤቶቹ የልጁን ብቃት ወይም የውጤት ደረጃ በትክክል የሚያሳዩ መሆናቸውን ወይም ፈተናዎቹ የሚለኩባቸውን የልጁን የስሜት ህዋሳት፣ የሰውነት እንቅስቃሴ ወይም የተመግባባት ችሎታዎች ከማሳየት ይልቅ ለመለካት የሚፈልጓቸውን ሌሎች ጉዳዮችን ነው፡፡ ለዚህ ብቸኛው ልዩ ሁኔታ ከህሎቶቹ ፈተናው ለመለካት ያሰበባቸው ሁኔታዎች ሲሆኑ ብቻ ነው።

ቸ. ደንቡን ያልተከተለ እና/ወይም መደበኛ ያልሆኑ እርምጃዎች መደበኛውን ግምገማ ለማሟላት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡

III. የግምገማ ሪፖርቶችን በተመለከተ የሚከተሉት ደረጃዎችና መመሪያዎች መከበር ይኖርባቸዋል፡-

ሀ. ተዛማጅ የባህሪ ምልከታዎች በሪፖርቱ ውስጥ መገለጽ ይኖርባቸዋል፡፡

ለ. ግምገማው በመደበኛ ሁኔታዎች ሳይካሄድ ቀርቶ ከሆነ ከመደበኛ ሁኔታዎች ምን ያህል እንደሚለያይ የሚገልጽ መግለጫ በግምገማ ሪፖርቱ ውስጥ ተካቶ መቅረብ አለበት፡፡

ሐ. ከተሰጡ ፈተናዎች የተገኙ የሁሉም ውጤቶች አባሪ ከሪፖርቱ ጋር እንዲቀርብ መደረግ አለበት፡፡ ፈተናዎች በባህላዊና የቋንቋ ሁኔታዎች ላይ ተመርኩዘው መመረጣቸውንና ውጤቶቹ ትክክለኛ ናቸው ተብሎ የሚታሰብ መሆኑን ሪፖርቱ የሚያረጋግጥ ትክክለኛ መግለጫ ማካተት ይኖርበታል፡፡

መ. የግለሰብ ገምጋሚዎች ግኝታቸውን ሪፖርት ለማድረግ ተጨባጭ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የስቴት ደንቦች እነዚህ ውሳኔዎች የሚደረጉት በባለብዙ ዲሲፕሊን ኮሚቴ ስለሆነ ገምጋሚው ለምደባ ወይም ብቁነት ልዩ ምክረ ሃሳቦችን ከማቅረብ መቆጠብ አለበት፡፡

ሠ. ለተጨማሪ ግምገማዎች ማንኛቸውም ምክሮች የትምህርት ቤቱ ቡድን ከግምት እንዲያስገባቸው መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

IV. የሚከተሉት ክፍያዎች፣ ወጪዎች እና የሚከፈልባቸው ተመኖች በAPS ተዘጋጅተዋል፦

| **የግምገማ አይነት** | **ክፍያዎች** |
|---|---|
| ሳይኮሎጂካል | እስከ $2,500 |
| ትምህርታዊ | እስከ $1,500 |
| ኒውሮሳይኮሎጂካል | እስከ $4,000 |
| ማህበረ-ባህላዊ | እስከ $600 |
| ንግግር/ቋንቋ | እስከ $950 |
| ኦኪፔሽናል ቴራፒ | እስከ $850 |
| አካላዊ ቴራፒ | እስከ $850 |
| የተግባር ባህሪ ግምገማ | እስከ $2,000 |
| አጋዥ ቴክኖሎጂ | እስከ $1,200 |
| ኦዲዮሎጂካል | እስከ $400 |
| የመስማት ሂደት | እስከ $1,000 |
| የእይታ ግምገማዎች | እስከ $400 |
| ሌሎች ግምገማዎች | እስከ $500 |

V. የክፍያ መጠየቂያ ደረሰኞችን ለማቅረብ የሚያስችሉ ሂደቶች፦

ሀ. ግምገማ አድራጊዎቹ የግምገማ ሪፖርቶችን ቅጂዎች ከዋናው ፊርማ ጋር **በአንድ ላይ** ለAPS የልዩ ትምህርት ቢሮ **እና** ለወላጅ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ የAPS የልዩ ትምህርት ቢሮ ዋናውን ሪፖርት ለተማሪው መሰረት ላደረገበት ትምህርት ቤት ቡድን የሚያቀርብ ይሆናል፡፡

ለ. የሚገመገመው ደረሰኝ፣ የW-9 ቅጽና የAPS ስታርስ አቅራቢ ማመልከቻ ወደ APS የልዩ ትምህርት ቢሮ በኢሜል iee@apsva.us ወይም በተረጋገጠ ፖስታ በሚከተለው አድራሻ መቅረብ አለባቸው።

Arlington Public Schools
Office of Special Education
Director of Elementary Special Education
2110 Washington Blvd., 2nd Floor
Arlington, Virginia 22204

እነዚህን መመሪያዎች በተመለከተ ጥያቄዎች ካልዎት፣ እባክዎን የAPS የአንደኛ ደረጃ ወይም የሁለተኛ ደረጃ የልዩ ትምህርት ዳይሬክተርን በ(703) 228-6040 ያግኙ፡፡